# ትንቢተ ዮናስ

## መግቢያ

### አሰያየሙ

መጽሐፉ የሚጠራው በዋናው ገጸ ባሕርይ በዮናስ ስም ሲሆን፣ የስሙም ትርጒም "ርግብ" ማለት ነው:: የስሜኑ መንግሥት "አእምሮ የሌለውና በቀላሉ የሚታለል" መሆኑን ለማመልከት ኤፍሬምን እንደተነጻጸረ ዘይቤ የተጠቀመበትን ከሆሴ 7፥11 ላይ ይመ:: በተጨማሪ መዝ 68፥13፤ 74፥19 እና ማብ ይመ::

### ጸሐፊው

ጸሐፊው ማን እንደ ሆነ በመጽሐፉ ውስጥ የተገለጸ ነገር ባይኖርም፣ በታሪክ ግን ነቢዩ ራሱ ማለትም በዛብሎን (ኢሱ 19፥10:13) በምትገኘው ጋትሔፌር (2ነገ 14፥25)የሚኖረው የአማቴ ልጅ (1፥1) ዮናስ እንደጻፈው ይነገራል:: ኤልያስንና ኤልሣዕን በሚመለከት ከተጻፈው ጽሑፍ ጋር ሲነጻጸር ብዙ የሚመሳሰልበት ሁኔታ ስለሚታይ፣ ስለ እነዚህ ነቢያት የጻፈው ሰው ይህንንም መጽሐፍ ጽፎ ይሆናል የሚል ግምት አለ፤ ጊዜውም በስምንተኛው ምዕተ ዓ.ቅ.ክ ሳይሆን አይቀርም :: (ከ1ነገ መግቢያ "ጸሐፊው፣ ምንጩና የተጻፈበት ጊዜ" የሚለውን ይመ)::

### ታሪካዊ ዳራው

ነቢዩ ዮናስ ባገለገለበት ዘመን በግማሽ ምእተ ዓመት ጊዜ ውስጥ (800-750 ዓ.ቅ.ክ) ዳግማዊ ኢዮርብዓም (793-753 ዓ.ቅ.ክ)፣ ከአንድ መቶ ዓመት በላይ በእስራኤልና በደማስቆ መካከል የነበረውን ጦርነት በድል በማጠናቀቅ በሰሜናዊው የእስራኤል መንግሥት ምድር ታላቅ ጀብዱ ሠራ፤ የእስራኤልንም ታሪካዊ ድንበር መለሰ:: ኢዮርብዓም እግዚአብሔር ረድቶት (2ነገ 14፥26-27) አሦር በ797 በወቅቱ የሶርያን ኀይል በማድቀቅ፣ በደማስቆ ላይ የተቀዳጀውን ድል ተጠቅሞበታል:: ከዚያን ጊዜ በፊት ግን የእስራኤል የግዛት መጠን ከማነሱም በላይ፣ የደማስቆ ንጉሥ በሰሜኑ (2ነገ 13፥7) መንግሥት የውስጥ ጉዳይ ገብቶ ይቆጣጠር ነበር:: ይሁን እንጂ አሦር በ797 በደማስቆ ላይ ከዘመተች በኋላ የእስራኤል ንጉሥ ዮአስ በደማስቆ ንጉሥ የተወሰደውን ግዛት አስመልሶ ነበር (2ነገ 13፥25):: በአሦር የተፈጠረው የውስጥ ችግር ዳግማዊ ኢዮርብዓም የእስራኤልን ሰሜናዊ የድንበር ግዛቶች ሙሉ ለሙሉ ለማስመለስ አስችሎታል:: ይህም እንኳ ሆኖ አሦር በዚህ ጊዜ በሰሜን በኩል የሚያስፈራ መንግሥት ሆኖ ቆይቶአል::

ይህን ሁኔታ አስመልክተው የእግዚአብሔር ነቢያት ለእስራኤል ይናገሩ ነበር:: በ797 ዓ.ቅ.ክ ገደማ ኤልሳዕ በደማስቆ ላይ ስለሚገኘው ድል ለእስራኤል ንጉሥ ተናግሮ ነበር (2ነገ 13፥14-19):: ከጥቂት ዓመታት በኋላም በዳግማዊ ኢዮርብዓም የተከናወነውን ድንበር የማስመለስ ጒዳይ አስመልክቶ ዮናስ ትንቢት ተናግሮአል (2ነገ14፥25)፤ እስራኤል ድል ካደረገች በኋላ ብዙ ሳይቈይ ባገኘችው ተጨማሪ የግዛት ሥልጣን ከመጠን በላይ መደሰትና መኩራራት ጀመረች:: ኤልሳዕና ዮናስ በተናገሩት የማጽናናት ቃል መሠረት እስራኤል ከውጭ ኀይል ተጽዕኖ ተላቃ ዕረፍት አገኘች፤ እግዚአብሔር ወዶ በሰጣት ታላቅ ድልና በረከት ተቀማጠለች (አሞ 6፥1)፤ ሃይማኖቷም ሌሎችን ሕዝቦች ጨለማ ሲውጣቸው እርሷ ግን በእግዚአብሔር ብርሃን የምትሆንበትን "የጌታን ቀን" በመጠባበቅ ላይ ያተኰረ ነበር (አሞ 5፥18-20)::

እግዚአብሔር ሕዝቡ እስራኤል ከደማስቆ አልፈው (አሞ 5፥27) ወደ አሦር (ሆሴ9፥3፤ 10፥6፤ 11፥5) እንዲሰደዱ ያደርጋል እንጂ ከእንግዲህ ሊታገሳቸው እንደማይችል ይነግሯቸው ዘንድ አሞጽንና ሆሴዕን የላከው (አሞ 7፥8፤ 8፥2) በዚህ ዐይነት ጊዜ ነበር:: ነነዌ ሊመጣ ካለው የእግዚአብሔር ቍጣ ትድን ዘንድ እንዲያስጠነቅቅ እግዚአብሔር ዮናስን የላከው በዚህ ጊዜ ነበር:: ዮናስ በአሞፅ ዘመን የነበረ በመሆኑ ለተጨማሪ መግለጫ ከአሞጽ መግቢያ "የተጻፈበት ቀንና ታሪካዊ ዳራው" የሚለውን ይመ::

### የተጻፈበት ጊዜ

ለአሕዛብ የተሰበከውን ስብከትና ሌሎች ምክንያቶ ስንመለከትም መጽሐፉ ከምርኮ በኋላ እንደተጻፈ ይገመታል፤ ስለዚህ በ612 ዓ.ቅ.ክ በነነዌ ላይ ከደረሰው ጥፋት በኋላ የተጻፈ ሳይሆን አይቀርም:: ይሁን እንጂ እነዚህ አስተያየቶች ይህን ያህል ወሳኝ አይደሉም:: ይህ ትረካ ኤልያስንና ኤልሳዕን በሚመለከት ከተጻፈው ጽሑፍ ጋር ተመሳሳይ እንደ ሆነ ተመልክተናል:: ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ነነዌ ከተገለበጠች በኋላ ከሆነ፣ የነነዌን ንስሓ መግባትና እንዳትጠፋ መደረጓን መጥቀስ አስፈላጊነቱ አጠያያቂ ነው:: በስምንተኛው ምዕተ ዓመት የእግዚአብሔርን ቃል ለአሕዛብ መናገር አያስፈልግም ብሎ ማለት ቀደም ሲል በነበሩበት ምዕተ ዓመታት ኤልያስና ኤልሳዕ አገልግሎታቸውን እስከ ባዕዳን ምድር ድረስ አስፍተው እንደ ነበር አለማስተዋል ነው (1ነገ 17፥24፤ 2ነገ 8፥1-17):: አሞጽም (760-750) በዘመኑ ለአሕዛብ ብቻ ሳይሆን ለእስራኤልም የእግዚአብሔርን የትድግና ሥራ የተናገረ ነቢይ ነበር (አሞ 1፥3-2፥16፤ 9፥7:12):: ምናልባት በ8ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ ይኸውም አሞጽና ሆሴዕ በይፋ የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ ከተናገሩ በኋላ በ722-

721 ሰማርያ በአሦር እጅ ከመውደቋ በፊት ተጽፎአል የሚለው የበለጠ አሳማኝ ሳይሆን አይቀርም::

**ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ**

ይህ መጽሐፍ እንደ ብዙዎቹ የብሉይ ኪዳን የትንቢት መጽሐፎች ሳይሆን፣ በአንድ ትንቢታዊ ተልእኮ ላይ ያተኮረ ታሪክ ነው:: በዚህ ተልእኮ ላይ ማተኮሩ፣ ስለ ኤልያስና ስለ ኤልሳዕ አገልግሎት በአንደኛና በሁለተኛ ነገሥት ውስጥ ከተጻፈው ታሪክ ጋር ይመሳሰላል፤ እንደዚሁም በኢሳይያስ፣ በኤርምያስና፣ በሕዝቅኤል ውስጥ ካሉ ከተወሰኑ ታሪኮች ጋር ይቀራረባል::

አብዛኛውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ላይ እንደሚታየው፣ ጸሐፊው ብዙውን ነገር በጥቂት ቦታ አሳጥሮ ጽፎአል፤ የመጽሐፉ ጠቅላላ ታሪክ የተገለጸው በአርባ ጥቅሶች ሲሆን፣ በተጨማሪም የዮናስን የምስጋና ጸሎት የሚገልጹ ስምንት በግጥም የተጻፉ ጥቅሶች ያካተተ ነው:: በይዘቱ ዕጥር ምጥን በማለቱ በግልጽነቱና በገጸ ባሕርይ አገላለጹ ከሩት መጽሐፍ ጋር ብዙ ይመሳሰላል::

"ድነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው" የሚለው የዮናስ ዐቢይ የንስሓ ጸሎት የታሪኩ ጡዘት ነው (1፥9፤ 2፥9፤ 4፥2):: ዮናስ ከነነዌ ወጣ ብሎ በጠራራ ፀሐይ በሜዳ ላይ ተቀምጦ ሳለ በመደምደሚያው ላይ የተጠቀሰው ዐረፍተ ነገር የእግዚአብሔር ቃል የመጨረሻና ወሳኝ እንደ ሆነ ይገልጻል::

ጸሓፊው ግልጽ በሆነ መንገድ አንድን ነገር ወክሎ በማቈም ሐሳብን የመግለጽ የአጻጻፍ ሥልት ይጠቀማል:: እግዚአብሔር የእስራኤል ጠላት ለሆነችው ነነዌ ያለው ፍቅር የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለአሕዛብ ሁሉ ያለውን ፍቅር ነው:: በአንጻሩም እምቢተኛው ዮናስ ያደረገው ነገር እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ስለ አላት መልካም ግንኙነት የምትቀናና የእግዚአብሔርንም ቸርነት ለአሕዛብ ለማካፈል ፈቃደኛ ያለመሆኗን የሚገልጽ ነው::

ይህ መጽሐፍ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሰፋ ያለ ዕቅድ እንዳለው ይገልጻል፤ ይኸውም እግዚአብሔር ለጠቅላላ ፍጥረቱ የሚገደው መሆኑን እስራኤል እንድትረዳና ይህንም ዐላማ ከግብ ለማድረስ የምትጫወተውን ሚና በሚገባ እንድታውቅ ነው::

**አስተዋፅኦ**

1. ዮናስ ከተልእኮው መሸሹ (ም 1-2)
   ሀ. ለዮናስ የተሰጠው ትእዛዝና ከዚያ መሸሹ (1፥1-3)
   ለ. ለአደጋ የተጋለጡት መንገደኞች ወደ አምላካቸው ያደረጉት ጩኸት (1፥4-6)
   ሐ. የዮናስ አልታዘዝም ባይነት ተጋለጠ (1፥6-10)
   መ. በዮናስ ላይ የተፈጸመው ቅጣትና ከጥፋት መዳኑ (1፥11-2፥1፤ 2፥10)
   ሠ. ለእግዚአሔር ያቀረበው የምስጋና ጸሎት (2፥2-9)
2. ዮናስ ሳይወድ ተልእኮውን መፈጸሙ (ም 3-4)
   ሀ. ዮናስ ወደ ነነዌ እንዲሄድ ዳግመኛ መታዘዙ፣ እርሱም ትእዛዙን መቀበሉ (3፥1-4)
   ለ. ለጥፋት የተጋለጠው የነነዌ ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ያደረገው የንስሓ ጸሎት (3፥5-9)
   ሐ. የነነዌ ሕዝብ ንስሓ ተቀባይነት ማግኘቱ (3፥10-4፥4)
   መ. ዮናስ ከጥፋት መዳኑ፣ የተሰጠውም ግሳጼ (4፥5-11)

## ዮናስ ከእግዚአብሔር ኰበለለ

1 የእግዚአብሔር ቃል ወደ አማቴ ልጅ ወደ
ዮናስ እንዲህ ሲል መጣ፤ 2 "ክፋቷ በእኔ
ፊት ወጥቶአልና ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ
ነነዌ ሂደህ፣ በእርሷ ላይ ስበክ።"
3 ዮናስ ግን ከእግዚአብሔር ፊት ኰበለለ፤
ወደ ተርሴስም ለመሄድ ተነሣ። ወደ ኢዮጴ
ወረደ፣ ወደዚያው ወደ ተርሴስ የምትሄድ
መርከብም አገኘ። የጕዞውንም ዋጋ ከከፈለ
በኋላ፣ ከእግዚአብሔር ፊት ወደ ተርሴስ ለመ
ኰብለል በመርከቢቱ ተሳፈረ። 4 እግዚአብሔ
ርም በባሕሩ ላይ ታላቅ ነፋስን ላከ፤ ከባድ
ማዕበልም ተነሥቶ መርከቢቱን አንገላታት፤
ልትሰበርም ተቃረበች። 5 መርከበኞቹ ሁሉ
ፈሩ፤ እያንዳንዱም ሰው ወደ አምላኩ ጮኸ፤
የመርከቢቱም ክብደት እንዲቀል፣ በውስጧ
የነበረውን ዕቃ ወደ ባሕሩ ጣሉት።
ዮናስ ግን ወደ መርከቢቱ ታችኛ ክፍል
ወርዶ ተኛ፤ በከባድም እንቅልፍ ላይ ነበር።
6 የመርከቢቱም አዛዥ ወደ እርሱ ሄዶ፣ "እን
ዴት ትተኛለህ? ተነሥና ስምባክህን ጥራ፤ እንጂ፤
ምናልባትም ያስበንና ከጥፋት ያድነን ይሆ
ናል" አለው።
7 ከዚያም መርከበኞቹ እርስ በርሳቸው፣ "ይህ
ክፉ ነገር በማን ምክንያት እንደ መጣብን ለማ
ወቅ፣ ኑ፣ ዕጣ እንጣጣል" ተባባሉ።

1፥1 2ነገ14፥25፤ ማቴ12፥39-41፤ 16፥4፤ሉቃ11፥29-32
1፥2 ዘፍ10፥11፤ ናሆ1፥1
1፥3 ዘፍ10፥4፤ ዘፀ4፥13፤ኢሱ19፥46፤ መዝ139፥7፤ ኤር20፥9፤አሞ3፥8፤ ሐሥ9፥36፡43
1፥4 መዝ107፥23-26
1፥5 ሐሥ27፥1819
1፥6 መዝ107፥28፤ ዮና3፥8
1፥7 ዘኍ32፥23፤ ኢሱ7፥10-18፤1ሳሙ 14፥42፤ምሳ16፥33

1፥1 *የእግዚአብሔር ቃል…መጣ፤* 3፥1 ይመ፤ ነቢዩ ለተቀበለው መገለጥ መለኮታዊ ምንጭ እንዳለው የሚያመለክት ሐረግ ነው (ለምሳሌ 1ነገ 17፥8፤ ኤር 1፥2፡4፤ ሆሴ1፥1፤ኢል 1፥1፤ ሐጌ 1፥1፡3፤ ዘካ1፥1፡7 ይመ)። *ዮናስ፤* ከመግቢያው፣ "የመጽሐፉ ርእስና ጸሓፊው" የሚለውን ይመ።

1፥2 *ታላቂቱ ከተማ፤* 3፥2፤ 4፥11 ይመ። እንዲሁም የ3፥3 ማብ ይመ። በዘፍ10፥11-12 መሠረት በመጀመሪያ በናምሩድ ከረሆቦት ኢር፣ ከካለህና ከሬሲን ጋር አንድ ላይ ሳትሠራ አት ቀርም፤ በዘመኑ በነበረው ትውፊት መሠረትም፣ በ612 ዓ.ቅ.ክ እስከ ወደቀችበት ጊዜ ድረስ "ታላቂቱ ከተማ" ተብላ ትታወቅ ነበር። (ከናሆም መጽሐፍ መግቢያ "ታሪካዊ ዳራው" የሚለውን ይመ) በ700 ዓ.ቅ.ክ ገደማ ሰናክሬም የአሦር ዋና ከተማ አደረጋት። ዮናስ ተወልዶ ካደገባት ከተማ ከጋት ሔፌር 800 ኪሎ ሜትር ያህል ትርቅ ነበር። *ክፋቷ በእኔ ፊት ወጥቶአልና፤* ከሰዶምና ከገሞራ ጋር ያወዳድሩ (ዘፍ 18፥20-21)። ከነነዌ ዐመፅ በቀር (3፥8)፣ "ክፉ መንገዳቸው" (3፥8፡10) በዮናስ መጽሐፍ ላይ አልተገለጸም። በኋላ ግን ናሆም የነነዌ ኀጢአት በእግዚአብሔር ላይ ክፋትን ማሤር (ናሆ 1፥11)፣ በጦርነት ጊዜም ጭከናና ዝርፊያ (ናሆ2፥12-13፤ 3፥1፡19)፣ ዝሙት አዳሪነትና ጥንቈላ (ናሆ 3፥4) እንዲሁም በንግድ አጭበር ብሮ መበዝበዝ እንደ ነበር ገልጸአል (ናሆ 3፥16)።

1፥3 *ኰበለለ፤* የዚህ ምክንያት በ4፥2 ተገልጾአል። ከእግዚአብሔር ለመኰብለል መሞከር ከንቱ እንደ ሆነ በመዝ 139፥7-9-10 ተጠቅሶአል። *ተርሴስም፤* ምናልባት በደቡብ ምዕራብ ስፓኝ የምትገኘው የታርቴሰስ ከተማና ከጂብራልተር አጠገብ ያለችው የፊንቃውያን የማዕድን ቅኝ ግዛት ነች። ዮናስ፣ የዓለም ዳርቻ ነው ተብሎ ወደሚታሰበው ከነነዌ ማዶ ወዳለው አቅጣጫ በመሄድ፣ ከእግዚአብሔር ከተሰጠው መለኮታዊ ተግባር ለመሸሽ ሞከረ።


*1፥4-5፤* የዮናስ ተልእኮ ለአረማውያን ፍርድ የማይቀር መሆኑን በመግለጽ የእግዚአብሔርን የማስጠንቀቂያ ቃል መናገር ቢሆንም፣ ወደ ነነዌ አልሄድም በማለቱ እነዚህን አረማውያን መርከበኞች ጭንቅ ውስጥ ከተታቸው።

1፥4 *እግዚአብሔርም…ታላቅ ነፋስን ላከ፤* በዮናስ ተልእኮ ውስጥ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ሥራ በሌሎች ነገሮችም ላይ ለምሳሌ፤ ዓሣ ነባሪው (ቍ 17)፣ የዮናስ መተፋት (2፥10)፣ የወይን ተክል (4፥6)፣ ትል (4፥7)፣ እንዲሁም የምሥራቅ ነፋስ (4፥8) ተገልጾአል።

1፥5 *ወደ አምላኩ፤* ከተለያዩ ወደቦች የመጡት መርከበኞች የተለያዩ የጣዖት አማልክትን ማምለካቸው ግልጽ ነው።

1፥6 *የመርከቢቱም አዛዥ ወደ እርሱ ሄዶ፤* አረማዊው የመርከብ አዛዥ በመርከቢቱ ላሉት ሁሉ ግድ መሰኘቱ፣ በእግዚአብሔር ከሚያምነው የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ለነነዌ ለመናገር እንቢተኛ ከሆነው ነቢይ ጋር የሚነጻጸር ነው።

1፥7 *ኑ፣ ዕጣ እንጣጣል፤* በቅርብ ምሥራቅ አገሮች ዕጣ መጣጣል በስፋት የተለመደ ሥርዐት ነበር። ትክክለኛው ዘዴ ግልጽ ባይሆንም፣ አብዛኛውን ጊዜ ከዕቃ ውስጥ ዕንጨቶችን ወይም ምልክት የተ



ትንቢተ ዮናስ

ዕጣም ተጣጣሉ፤ ዕጣውም በዮናስ ላይ ወደቀ።
8 ከዚያም፣ “ይህ ሁሉ አስጨናቂ ነገር
በማን ምክንያት እንደ መጣብን ንገረን፤ ሥራህ
ምንድን ነው? ከወዴትስ መጣህ? አገርህስ
የት ነው? ከየትኛውስ ሕዝብ ነህ?”አሉት።
9 እርሱም፣ “እኔ ዕብራዊ ነኝ፤ የብስንና
ባሕርን የፈጠረውን፣ የሰማይን ስምባክ እግዚ
አብሔርን አመልካለሁ” አለ።
10 እርሱ አስቀድሞ ነግሮአቸው ስለ ነበር፣
ከእግዚአብሔር እንደ ኰበለለ ዐወቁ፣ ስለዚህም
በሁኔታው በመደንገጥ፣ “ይህ ያደረግኸው
ምንድን ነው?” አሉት።
11 የባሕሩም ማዕበል እጅግ እየበረታ ስለ
ሄደ፣ “ባሕሩ ጸጥ እንዲልልን በአንተ ላይ
ምን ብናደርግ ይሻላል?” አሉት።
12 እርሱም፣ “ይህ ታላቅ ማዕበል በእኔ ምክን
ያት እንደ መጣባችሁ ዐውቃለሁ፤ አንሥታ
ችሁ ወደ ባሕሩ ጣሉኝ፤ ባሕሩም ጸጥ ይላል”
አላቸው።
13 ሰዎቹ ግን ባላቸው ኀይል እየቀዘፉ
ወደ የብስ ለመጠጋት ሞከሩ፤ ይሁን እንጂ
አልቻሉም፤ ባሕሩ የባሰ ይናወጥ ነበርና።
14 “እግዚአብሔር ሆይ፤ እባክህ በዚህ ሰው ነፍስ
ምክንያት አታጥፋን፤ የዚህ ንጹሕ ሰው ደምም
በእኛ ላይ አይሁን፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ
የወደድኸውን አድርገሃልና” ብለው ወደ
እግዚአብሔር ጮኹ። 15 ከዚያም ዮናስን
ይዘው ወደ ባሕሩ ጣሉት፤ ባሕሩም ከመና
ወጥ ጸጥ አለ። 16 ሰዎቹም እግዚአብሔርን
እጅግ ፈሩ፤ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትም
አቀረቡ፤ ለእርሱም ስእለትን ተሳሉ።
17 እግዚአብሔር ግን ዮናስን የሚውጥ ትልቅ
ዓሣ አዘጋጀ፤ ዮናስም በዓሣው ሆድ ውስጥ
ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት አደረ።

1፥9 ዘፍ1፥9፤ነህ 9፥6፤መዝ96፥9፤ዳን 2፥18፤ሐሥ17፥24
1፥12 2ሳሙ 24፥17፤ 1ዜና21፥17
1፥13 ምሳ21፥30
1፥14 ዘዳ21፥8፤ ዳን4፥35
1፥15 መዝ107፥29፤ ሉቃ8፥24
1፥16 ዘኁ30፥2፤ መዝ66፥1314፤ማር 4፥41
1፥17 ዩና4፥6:7፤ ማቴ12፥40፤16፥4፤ ሉቃ11፥30
2፥2 መዝ18፥6፤ 86፥13፤120፥1፤ ሰቆ3፥55
2፥3 2ሳሙ22፥5፤ መዝ42፥7፤88፥6
2፥4 1ነገ8፥48፤ መዝ31፥22፤ኤር7፥15

## የዮናስ ጸሎት

2 ዮናስ በዓሣው ሆድ ውስጥ ሆኖ ወደ
ስምባኩ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤

2 እንዲህም አለ፤
“ተጨንቄ ሳለሁ ወደ እግዚአብሔር
ተጣራሁ፤
እርሱም መለሰልኝ፤
ከመቃብሩም[ሀ] ጥልቅ ርዳታን ፈልጌ
ተጣራሁ፤
አንተም ጩኸቴን ሰማህ።
3 ጥልቅ ወደ ሆነው፣
ወደ ባሕሩ መካከል ጣልኸኝ፤
ፈሳሾችም ዙሪያዬን ከበቡኝ[ለ]፤
ማዕበልህና ሞገድህ ሁሉ፣
በላዬ አለፉ።
4 እኔም፣ ‘ከፊትህ ጠፋሁ፣
ነገር ግን እንደ ገና፣
ወደ ቅዱስ መቅደስህ፣
እመለከታለሁ’ አልሁ።

[ሀ]2 የዕብራይስጡ ትርጒም ሲዖል ይላል።
[ለ]5 *“ውሃዎች በጕሮሮዬ ነበሩ”* የሚሉ አሉ

ደረገባቸውን ጠጠሮች በማውጣት ዕጣ ከሚጣልበት ጒዳይ ላይ ይጥሉ ነበር። *ዕጣውም በዮናስ ላይ ወደቀ፤* በዕጣው ፍርድ እግዚ አብሔር ወንጀለኛውን ገለጠው (ከኢሱ 7፥14-26፤ ከ1ሳሙ 14፥38-44፤ ከምሳ 16፥33 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፥9 *ዕብራዊ፤* የዘፍ 14፥13 ማብ ይመ። *የብስንና ባሕርን የፈጠረውን የሰማይን አምላክ፤* መርከበኞቹ ዮናስ የተናገረው ስለ ትልቅ አምላክ እንደ ሆነ ሳይረዱ አልቀረም። በጥንት ዘመን የቅርብ ምሥራቅ ሃይማኖቶች በአብዛኛው ከፍተኛው አምላክ የባሕሮች ጌታ ነው ብለው ያምኑ ስለነበር፣ በነበሩበት ሁኔታ ውስጥ የተከሠተው ነገር ይህንን እውነት አጽንቶላቸዋል (የኢሱ 3፥10 ማብ ይመ)። ይህ የዮናስ የመጀመሪያ ንስሓ ነው፤ እንደ መጀመሪያው ንስሓ ሁለተኛውም ንስሓ፣ (ከ2፥9፤ 4፥2) ፍጹም እውነት ነበር። እምነቱ ትክክል ቢሆንም እንኳ፣ ዮናስ ለነነዌ የተሰጠውን መለኮታዊ ተልእኮ ለመፈጸም እምቢተኛ ሆነ።

1፥10 *ይህ ያደረግኸው ምንድነው?* ይህ መልስ አዘል ጥያቄ በዮናስ ላይ እንደ ክስ ይቈጠራል።

1፥12 *አንሥታችሁ ወደ ባሕሩ ጣሉኝ፤* በፍርሀት የተሸበሩትን መርከበኞች ሕይወት ለማትረፍ የዮናስ ለሞት መዘጋጀት፣ ራቅ ካለ ስፍራ ሆኖ ከተማዪቱ ስትጠፋ ለማየት ቢያንስ እንደምትጠፋ ተስፋ በማድረግ (4፥5 ይመ)፣ በልበ ደንዳናነት ካደረገው ሽሽት ጋር የሚነጻጸር ነው።

1፥13 *ባላቸው ኀይል እየቀዘፉ፤* የዕብራይስጡ አገባብ ሥራው የቱን ያህል አድካሚ መሆኑን ለማመልከት እጅግ ሥዕላዊ የሆነ አገላለጽ ያለውን ቃል ይጠቀማል፤ ይኸውም፤ “በመቅዘፊያ መቈፈር” የሚል ትርጒም አለው። መርከቧ በነፋስ ኀይል ወይም በመቅዘፊያ፣ አሊያም በሁለቱ ልትነዳ ትችላለች። መርከበኞቹ ዮናስን ወደ ባሕሩ ለመወርወር ማንገራገራቸው ዮናስ ነነዌ ከሚ መጣባት ፍርድ እንድትጠነቀቅ ለመናገር ፈቃደኛ ካለመሆኑ ጋር በእጅጉ የሚነጻጸር ነው።

1፥16 *እግዚአብሔርን እጅግ ፈሩ፤* መርከበኞቹ ሌሎችን አማልክት ሁሉ ያወገዙበት ምንም ማስረጃ የለም (ንዕማንን ከ2ነገ 5፥15 ጋር ያነጻጽሩ)። ጥንት የነበሩ አረማውያን የሌሎች ብዙ አማልክትን ህልዎትና ኀይል ለማስተናገድ ዝግጁ ነበሩ። ስለዚህ መርከበኞቹ ቢያንስ ያሉበት ሁኔታ በእስራኤል አምላክ ቍጥጥር ሥር እንደሆነ፤ እርሱ ማዕበሉን እንዳስነሣና ጸጥ እንዳደረገ፣ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሊታወቅና ሊሰገድለት የሚገባው እርሱ መሆኑን ተገንዝበዋል።

1፥17 *እግዚአብሔር...አዘጋጀ፤* ይህ ባሕርይ ገላጭ የሆነ ሐረግ በ4፥6-8 ላይም ይገኛል። *ትልቅ ዓሣ፤* በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው የዕብራይስጡ ቃልና በማቴ 12፥40 የተጠቀሰው የግሪክ ቃል ትልቅ ዓሣን በሚያሳይ መልክ በጥቅሉ የተገለጸ በመሆኑ፣ የግድ ዓሣ ነባሪን አያመለክትም። ይህ ትልቅ ዓሣ በአሞ 9፥3 ከተጠቀሰው ከክፉው የባሕር እባብ በጥንቃቄ ተለይቶ ተገልጾአል፤ በተረፈ “ሌዋታን” (ኢሳ 27፥1) እና “የጥልቁ አውሬ ”(ኢዮ 7፥12፤ መዝ 74፥13፤ ሕዝ 32፥2 ይመ) ተብሎ ተጠርቶአል። *ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት፤* በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ሐረግ፣ በማቴ 12፥40 ላይ እንዳለው አንድ ሙሉ ቀንንና የሌሎች ሁለት ቀኖችን ሰዓታት ጨምሮ አንድ የተወሰነ ጊዜን የሚያመለክት ነው። (የማቴ 12፥40፤ የሉቃ 9፥28፤ የ1ቆሮ 15፥4 ማብ ይመ)። ያም ሆነ ይህ አዲስ ኪዳን ዮናስ ያለፈበትን ሁኔታ፣ ሦስት ቀንና ሌሊት በመቃብር ሳያልፈው ለክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አምሳያ አድርጎ ያቀርበዋል። (ማቴ 12፥40፤ ማቴ 16፥4፤ ሉቃ 11፥29-32 ይመ)።

2፥2-9፤ በባሕር ውስጥ እያለ እንዳይሞት ትድግናን ያገኘ ዘንድ የቀረበ የምስጋና መዝሙር ነው። ዮናስ ወደ ጥልቆ እየሰ መጠ ሲሄድ፣ ለርዳታ የጸለየውን ጸሎት አስታወሰ። ስለፈጸመው በደል ሞት የሚገባው ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ግን የተለየ ምሕ ረት እንዳደረገለት ስላወቀ፣ ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው አክብ ሮት ከፍ ብሎበታል። የዚህ መዝሙር ቋንቋ፣ ዮናስ የዳዊትን የምስጋና መዝሙሮች ሥነ ጽሑፍ ጠንቅቆ እንደሚያውቅ ያመለ ክታል።

2፥2 *ከመቃብሩም፤* ዮናስ በባሕር ውስጥ የሞተ ያህል እንደተሰማው የሚያመለክት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው (መዝ 18፥5፤ 30፥3 ይመ)፤ የዘፍ 37፥35 ማብ ይመ።

2፥3 *ጣልሽኝ...ማዕበልህና፤* ዮናስ መርከበኞቹ (1፥15) የእግ ዚአብሔር ፍርድ ማስፈጸሚያ መሣሪያዎች መሆናቸውን ተገን ዝቦአል።

2፥4 *ነገር ግን እንደገና ወደ ቅዱስ መቅደስህ እመለከ ታለሁ፤* ተመሳሳይ የሆነ በተስፋ የመጠባበቅ ሁኔታ በዳዊት የጸሎት መዝሙሮችም ውስጥ ይገኛል (ለምሳሌ መዝ 5፥7፣ 27፥4)። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው፣ “ቤተ መቅደስ” በኢየሩሳሌም ያለውን ቤተ መቅደስ የሚያመለክት ይመስላል፤ በቍ 7 የተጠቀሰው ግን በሰ ማይ ያለውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ የሚያመለክት

5ውሃ እስከ ዐንገቴ አጠለቀኝ፤
ጥልቁም ከበበኝ፤
የባሕርም ዐረም በራሴ ላይ ተጠመጠመ።
6ወደ ተራሮች መሠረት ሰመጥሁ፤
የምድርም በር ለዘላለም ተዘጋብኝ፤
*እግዚአብሔር* ስምላኬ ሆይ፤
አንተ ግን ሕይወቴን ከጕድጓድ አወጣህ።
7“ነፍሴ በዛለች ጊዜ፣
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተን ዐሰብሁ፤
ጸሎቴም ወደ አንተ፣
ወደ ቅዱስ መቅደስህ ዐረገች።
8“ከንቱ በሆኑ ጣዖቶች ላይ የሚንጠለጠሉ፣
ሊያገኙ የሚገባቸውን ጸጋ ያጣሉ።
9እኔ ግን በምስጋና መዝሙር፣
መሥዋዕት እሠዋልሃለሁ፤
የተሳልሁትንም እሰጣለሁ፤
ድነት *ከእግዚአብሔር* ዘንድ ነው።”
10*እግዚአብሔርም* ዓሣውን አዘዘው፤ ዮናስንም
በደረቅ ምድር ላይ ተፋው።

**ዮናስ ወደ ነነዌ ሄደ**

**3** *የእግዚአብሔርም* ቃል ለሁለተኛ ጊዜ
እንዲህ ሲል ወደ ዮናስ መጣ፤
2“ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነነዌ ሄደህ የም
ነግርህን መልእክት ስበክላት።”
3ዮናስም *የእግዚአብሔርን* ቃል ታዘዘ፤ ወደ
ነነዌም ሄደ። በዚህ ጊዜ ነነዌ ታላቅ ከተማ
ነበረች፤ እርሷንም ከዳር እስከ ዳር ለመጐብ
ኘት ሦስት ቀን ያስፈልግ ነበር። 4ዮናስም
ወደ ከተማዪቱ ገብቶ የመጀመሪያውን ቀን
ከተጓዘ በኋላ “ነነዌ በአርባ ቀን ውስጥ ትገ
ለበጣለች” ብሎ ዐወጀ። 5የነነዌም ሰዎች እግ
ዚአብሔርን አመኑ፤ ጾምንም ዐወጁ፤ ሰዎቹም
ሁሉ ከትልቁ እስከ ትንሹ ማቅ ለበሱ።
6ወሬውም ወደ ነነዌ ንጉሥ በደረሰ ጊዜ፣
ከዙፋኑ ወረደ፤ ልብሱንም አወለቀ፤ ማቅም
ለብሶ በዐመድ ላይ ተቀመጠ። 7ከዚያም
እንዲህ ሲል በነነዌ ዐዋጅ አስነገረ፤

“ከንጉሡና ከመሳፍንቱ የወጣ ዐዋጅ፤

ማንም ሰው ወይም እንስሳ፣ የከ
ብት መንጋም ሆነ የበግ መንጋ፣
ምንም ነገር አይቅመስ፤ አይብላ፤
ውሃም አይጠጣ። 8ነገር ግን ሰውም
እንስሳም ማቅ ይልበስ፤ ሁሉም አጥ
ብቆ ወደ እግዚአብሔር ይጩኽ፤ ሰዎ
ችም ሁሉ ክፉ መንገዳቸውንና የግፍ
ሥራቸውን ይተዉ። 9እኛ እንዳንጠፋ
እግዚአብሔር ራርቶ ከጽኑ ቍጣው
ይመለስም እንደ ሆነ ማን ያውቃል?”

10እግዚአብሔርም ምን እንዳደረጉና ከክፉ
መንገዳቸውም እንዴት እንደ ተመለሱ ባየ
ጊዜ ራራላቸው፤ በእነርሱም ላይ ሊያመጣ
ያሰበውን ጥፋት አላደረገም።

**ዮናስ እግዚአብሔር ምሕረት በማድረጉ ተቈጣ**

**4** ዮናስ ግን ፈጽሞ አልተደሰተም፤ ስለዚህም
ተቈጣ። 2ወደ *እግዚአብሔርም* እንዲህ
ብሎ ጸለየ፤ “*እግዚአብሔር* ሆይ፤ በአገሬ ሳለሁ
የተናገርሁትስ ይህን አልነበረምን? ፈጥኜ
ወደ ተርሴስ ለመኰብለል የተነሣሁትም ለዚሁ
ነበር፤ አንተ ቸርና ርኅሩኅ፣ ምሕረትህ የበዛ
ከቍጣ የራቅህ አምላክ፣ ጥፋትንም ከማም
ጣት የምትመለስ እንደ ሆንህ ዐውቃለሁ።
3አሁንም *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ነፍሴን ውሰድ፤
ከምኖር መሞት ይሻለኛልና።”
4*እግዚአብሔር* ግን፣ “በውኑ ልትቈጣ
ይገባሃልን?” አለው።
5ዮናስም ከከተማዪቱ ወጥቶ በስተ ምሥራቅ
በአንድ ስፍራ ተቀመጠ። በዚያም ለራሱ ዳስ ሠራ፤

2፥5 መዝ69፥12
2፥6 ኢዮ17፥16፤ 28፥9፤33፥18፤ መዝ30፥3
2፥7 2ዜና30፥27፤ መዝ11፥4፤18፥6፤ 77፥11-12
2፥8 ዘዳ32፥21፤ 1ሳሙ12፥21
2፥9 ዘፀ15፥2፤ዘኍ 30፥2፤መዝ3፥8፤42፥4 ፤50፥14፡23፤116፥14፤ መክ5፥4-5፤ዕብ13፥15
3፥1 ዮና1፥1
3፥4 ኤር18፥7-10
3፥5 ዳን9፥3፤ማቴ 11፥21፤12፥41፤ሉቃ 11፥32
3፥6 አስ4፥1-3፤ ኢዮ2፥8፡13፤ ሕዝ27፥30-31
3፥7 2ዜና20፥3፤ ዕዝ10፥6
3፥8 ኢዮ16፥17፤ መዝ130፥1፤ኤር 7፥3፤25፥5፤ና1፥6
3፥9 2ሳሙ12፥22፤ መዝ85፥3፤ኤር18፥8፤ ኢዩ2፥14
3፥10 ዘፀ32፥14፤ ኤር18፥8፤አሞ7፥6
4፥1 ቍ4፤ ማቴ20፥11፤ሉቃ 15፥28
4፥2 ዘፀ22፥27፤ዘኍ 14፥18፤ዘዳ4፥31፤ መዝ86፥5፡15፤103፥8 ፤ኤር20፥78፤ ኢዩ2፥13
4፥3 ዘኍ11፥15፤ ኢዮ7፥15፤ኤር8፥3
4፥4 ዘፍ4፥6፤ ማቴ20፥11-15

ነው። እስራኤላውያን እነዚህን ሁለት የእግዚአብሔር ማደሪያዎች ሳይነጣጥሉ ይመለከቱአቸዋል (1ነገ 8፥38-39 ይመ)።

2፥6 *ከጕድጓድ፤* ከመቃብር ለማለት ነው (የቍ 2 ማብ ይመ፣እንዲሁም መዝ 30፥3 ይመ)።

2፥9 *የተሳልሁትንም፤* በመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ውስጥ ጸሎቶች በአብዛኛው የምስጋና መሥዋዕትን በያዙ ስእለቶች የታ ጀቡ ናቸው (ለምሳሌ መዝ 50፥14፤ 56፥12፤61፥8፤65፥1፤66፥13-14፤ 116፥12-19)። *ድነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፤* የዮናስ በከፍተኛ ደረጃ ያቀረበው የምስጋና ጸሎት ነው። ይህ የዮናስ ሁለተኛ የንስሓ ቃል ሲሆን (የ1፥9 ማብ ይመ)፣ የመጽሐፉ ሥነ ጽሑፋዊ ማእከል ነው።

3፥2 *የምነግርህን መልእክት ስበክላት፤* ነቢይ የእግዚአብሔርን መልእክት የሚያቀርብ እንጂ በቅድሚያ ስለሚመጣው ሁኔታ የሚና ገር አይደለም።

3፥3 *ታዘዘ፤* ይታዘዝ እንጂ የነነዌ ሰዎች እንዲጠፉ ይፈልግ ነበር (4፥1-5)። *ታላቅ ከተማ፤* ከተማዪቱ ከ120,000 የሚበልጡ ኗሪዎች እንደነበሩባት የሚናገረውን 4፥11 ይመ። የሥነ ቅርስ ተመራማሪዎች ቍፋሮ ኋለኛዪቱ የነነዌ የንጉሥ ከተማ ዙሪያዋ 12ኪ.ሜ ያህል እንደነበር ያመለክታል። ሆኖም፣ “ለመጐብኘት ሦስት ቀን ይወስዳል” የሚለው አባባል ሰፊ ቦታን የሸፈነች ከተማ መሆኗን ያመለክታል። ይኸውም በዘፍ10፥11-12 እንደ ተጠቀሰው አራቱን ከተሞች ማለትም ነነዌ፣ ረሆቦት፣ ካለህና ሬሴንን የሚያጠቃልል ሊሆን ይችላል። የታላቋ የነነዌ ከተማ ዙሪያዋ 96 ኪሎ ሜትር ይሸፍናል። በሌላም በኩል፣ “ሦስት ቀን” የሚለው አባባል የመካከለኛ ርዝመት ርቀትን ለመ ግለጽ የሚውል የተለመደ አባባል ሳይሆን አይቀርም (ዘፍ 30፥36፤ ዘፀ 3፥18፣ኢያሱ 9፥16-17 ይመ)።

3፥5-6 *ጾምንም ዐወጁ ... ማቅ ለበሱ...በዐመድ ላይ ተቀመጠ፤* በንስሓ ራስን የማዋረድ የተለመደ ምልክት ነው (1ነገ 21፥27፤ ነህ 9፥1 ይመ)።

3፥5 *እግዚአብሔርን አመኑ፤* የነነዌ ሰዎች በእውነት ወደ እግዚአብሔር ተመልሰዋል ማለት ሊሆን ይችላል (ከማቴ 12፥41 ጋር ያነጻጽሩ)። በሌላ በኩል በእግዚአብሔር ማመናቸው መርከበ ኞቹ ከነበራቸው ፈሪሀ እግዚአብሔር (የ1፥16 ማብ ይመ) ይህን ያህል የጠለቀ ላይሆን ይችላል። ቢሆንም ግን የነቢዩን ማስጠንቀ ቂያ ሰምተው ርምጃ ወስደዋል።

3፥6 *ወደ ነነዌ ንጉሥ፤* የአሦር ንጉሥ ነው።

3፥8፤ የቤት እንስሳትን መጨመር የተለመደ አልነበረም፤ የነነዌ ሰዎች የእግዚአብሔርን ምሕረት በአስቸኳይ እንደፈለጉም ይገልጻል።

3፥9፤ እግዚአብሔር ንስሓ ለሚገባ ሰው ሊመጣ ያለውን ቅጣት በማስቀረት ዘወትር ምሕረት ያደርጋል።

4፥1 *ተቈጣ፤* እግዚአብሔር ለእስራኤል ጠላት በመራራቱ ዮናስ እጅግ ተቈጣ። እግዚአብሔር በጎነቱን ለእስራኤል ብቻ እንጂ ለአሕዛብ እንዲገልጥ አልፈለገም።

4፥2 *ርኅሩኅ፤ ምሕረትህ የበዛ፤* ዘፀ 34፥6-7 ማብ ይመ። ዮናስ የተለመደውን የንስሓ አገላለጽ ሥርዐት ይከተላል (የ1፥9 ማብ ይመ)። *ከቍጣ የራቅህ፤* በአንጻሩ ግን ዮናስ ፈጥኖ ተቈጥቶአል (ቍ 19)።

4፥3 *ነፍሴን ውሰድ፤* ነቢዩ ኤልያስ በ1ነገ 19፥4 ከተናገረው ጋር ያነጻጽሩ። እግዚአብሔር ምሕረቱን ለነነዌ ቢገልጥ ዮናስ እስራ ኤል በእግዚአብሔር ዘንድ ያላትን ተወዳጅነት የምታጣ መሰለው። ከጥቂት ጊዜ በፊት ዮናስ ትድግናን በማግኘቱ ተደስቶ ነበር፤ አሁን ግን ነነዌ ስላልጠፋች ሞትን ተመኘ።

4፥5 *ዳስ፤* ይህ ዳስ ከሰጠው ጥላ ይልቅ በሚቀጥለው ቍጥር እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር ያዘጋጀው ቅል የበለጠ ጥላ እንደሚሰጥ

በከተማዪቱም የሚሆነውን ለማየት ከዳሱ ጥላ
ሥር ተቀመጠ። 6*እግዚአብሔር* አምላክም የቅል
ተክል አብቅሎ፣ የዮናስ ራስ ጥላ እንዲያገኝና
ሙቀትም እንዳያስጨንቀው ከበላዩ እንዲ
ያድግ አደረገ፣ ዮናስም ስለ ቅሉ እጅግ ደስ
አለው። 7ነገር ግን በሚቀጥለው ቀን በማለዳ
እግዚአብሔር ትል አመጣ፤ ትሉም ቅሉን በላ፤
ቅሉም ደረቀ። 8ፀሓይ ስትወጣ፣ እግዚአብሔር
የሚያቃጥል የምሥራቅ ነፋስ አመጣ፤ ፀሓ
ዩም የዮናስን ራስ አቃጠለ፤ እርሱም ተዝለፈ
ለፈ፤ መሞትም ፈልጎ፣ 'ከመኖር መሞት ይሻለ
ኛል" አለ።
9እግዚአብሔር ግን ዮናስን፣ "በውኑ ስለ ቅሉ
ልትቈጣ ይገባሃልን?" አለው።
እርሱም፣ "በእርግጥ እስከ ሞት ልቈጣ
ይገባኛል" አለ።
10*እግዚአብሔር* ግን እንዲህ አለው፤ "አንተ
እንዲበቅል ወይም እንዲያድግ ላልደከምክ
በት ለዚህ ቅል እጅግ አዝነሃል፤ በአንድ
ሌሊት በቀለ፤ በአንድ ሌሊትም ደረቀ።
11ታዲያ፣ እኔ ቀኝና ግራቸውን ለይተው
መናገር የማይችሉ፣ ከአንድ መቶ ሃያ ሺህ
በላይ ሰዎችና አያሌ እንስሶች ለሚኖሩባት
ለታላቋ ከተማ ለነነዌ ማዘን አይገባኝምን?"

4፥6 ዮና1፥17
4፥7 ኢል1፥12
4፥8 1ነገ19፥4
4፥9 ቁ4
4፥11 ዮና1፥2፤ 3፥2፡10

ተገልጸአል። የሚሆነውን ለማየት፤ ዮናስ አሁንም የነነዌን መጥፋት ተስፋ ያደርግ ነበር።

4፥6 *እግዚአብሔር አምላክም ... አደረገ* ይህ ባሕርይ ጉዳዩ ሐረግ በተጨማሪ በቊ 7-8፣ 1፥17 ላይም ይገኛል። *የቅል ተክል፤* ዘይት ከሚሰጡ ተክሎች አንዱ ሆኖ፣ ዐሥራ ሁለት ጫማ ያህል ከፍታና ሰፋፊ ቅጠሎች ያሉት ትንሽ ዛፍ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር በምሕረቱ፣ እልኸኛና ልበ ደንዳና ለሆነው ለእርሱ ነቢይ ምቾትን አበዛለት።

4፥8 *መሞት ይሻለኛል፤* የቊ 3 ማብ ይመ።

4፥10 *በአንድ ሌሊት በቀለ፤ በአንድ ሌሊትም ደረቀ፤* አሁን ታይቶ ወዲያው የሚጠፋን ነገር የሚያመለክት ነው።

4፥11 *ቀኝና ግራቸውን ለይተው መናገር የማይችሉ፤* እንደ ትንንሽ ልጆች (ከዘዳ 1፥39፤ ከኢሳ7፥15-16 ጋር ያነጻጽሩ) የነነዌ ሰዎች የእግዚአብሔር የአባትነት ርኅራኄ ያስፈልጋቸዋል። *አያሌ እንስሶች፤* የእግዚአብሔር ርኅራኄ ለቤት እንስሳትም ጭምር ነው። *ማዘን አይገባኝምን?* እግዚአብሔር በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ እንደ ተናገረ ሁሉ (1፥1)፣ ከዚህም ላይ በመጨረሻ ይናገራል። ለዮናስ የሰጠው ተልእኮ ለነነዌ ሰዎች ያሳየውን ምሕረትና ርኅራኄ የሚያመለክት ሲሆን፣ ለዮናስ የተነገረው የመጨረሻው ቃል ደግሞ እግዚአብሔር ለሰውና ለእንስሳ ማለትም ለፍጥረት ሁሉ ግድ መሰኘቱን በአጽንዖት የሚያመለክት ነው። "እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ሰውንም እንስሳትንም ታድናለህ" (መዝ 36፥6፣ ነህ 9፥6፣ መ145፥16 ይመ)፤ ይህም ብቻ ሳይሆን፣ "ከመንገዳቸው ተመልሰው በሕይወት እንዲኖሩ እንጂ በክፉዎች ሞት ደስ አልሰኝም" (ሕዝ 33፥11፣ ሕዝ 18፥21-23 ይመ) ብሎሃል። ከጥንት ጀምሮ ዮናስና የአገሩ ሰዎች እግዚአብሔር ለእስራኤል ባለው ልዩ ምሕረት ደስ ሲሰኙ በአንጻሩ በጠላቶቻቸው ላይ እንዲደርስ የሚመኙት የእርሱን ቍጣ ብቻ ነው፤ በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር እንዲህ ዐይነቱን ደንዳናነት በመንቀፍ የእርሱን የተትረፈረፈ ደግነት ያውጃል። እንዲህ ዐይነቱን ጥንካሬና ክፋት በዚህ ስፍራ ሲገሥጽ፣ የራሱን ምሕረትና በጎነት ግን በይፋ ይናገራል።